በ ወንጌል አማኞች
የምርጦቹ 7000
ቤተክርስቲያን ሮም



# የእግዚአብሔር መንግስት ራዕይ ዘሮች

***March 2014***

**በ ወንጌል አማኞች**

# የምርጦቹ 7000 ቤተክርስቲያን

## ስያሜ

***"ለበአል ያልሰገዱትን ሰባት ሺህ ሰወች ለእኔ አስቀርቻለሁ። እንደዚሁም በአሁኑ ዘመን ደግሞ በፀጋ የተመረጡ ቅሬታወች አሉ።"*** (ሮሜ 11፤4-5)

ስም የአንድን አካል ማንነትና ተግባር የሚገልጥ መጠሪያ ነው:: የምርጦቹ 7000 ቤተክርስቲያን ስያሜ የፍፁሙን ሰው ማንነትና እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያኗ የሰጣትን ተግባርና ሃላፊነት በሚገልጥ መልኩ የተቀመጠ ነው:: የቤተክርስቲያኗ ስያሜ ከሌላው የክርስቶስ አካል ቤተክርስቲያን ልዩ /Special/ መሆኗን የሚጠቁም አልያም በውስጧ ያለውን የአማኝ ቁጥር ወይም የአባላት ብዛት /Members/ የሚወስን አይደለም::

የምርጦቹ 7000 ቤተክርስቲያን ስያሜ መነሻ ሀሳብ በ1ኛ ነገስት 19፡18 ላይ የሚገኝ ሲሆን እንደሚከተለው ይነበባል ***<<እኔም ከእስራኤል ጉልበታቸውን ለባአል ያላንበረከኩትን ሁሉ በአፋቸውን ያልሳሙትን ሁሉ ሰባት ሺህ (7000) ሰዎች ለእኔ አስቀራለሁ>።*** በዚህ ቃል ውስጥ እንደምናየው እነዚህ ሰባት ሺህ ሰዎች የሚወክሉት ብዛትን ሳይሆን በእስራኤል (በቤተክርስቲያን) መካከል አንድ የተለየ አይነት አቋምና ተልዕኮ የያዙ የሰዎችን አይነት ነው፡፡ ይኸዉም፡- ለዲያቢሎስ ዛቻና ማስፈራሪያ፣ ለዚህ ዓለም ፍልስፍናና መንፈስ፤ እንዲሁም ለባዕድ አምልኮ ያልተንበረከኩ፤ ይልቅ በምድሪቱ ያለውን ድርቀት በሰማይ ጠል የሚያረሰርሱ፣ የጥፋት የክፍትና የባዕድ አምልኮ መሰዊያዎችን በመንፈስ የሚያፈራርሱ፤ የእግዚአብሔርን ብቸኛ አምላክነት፣ የክብሩንም ታላቅነት በህይወት፣ በስራና በንግግር የሚገልጡ፣ ፅድቅን በቤተክርስቲያን፣ በምድርና በትውልድ ላይ የሚያውጁ የእግዚአብሔር ቅሬታዎችን የሚያሳይ ወይንም የሚገልጥ ነው፡፡ የምርጦቹ 7000 ቤተክርስቲያን ስያሜም ከዚህ መልዕክትና መንፈስ የመነጨ ነው፡፡

## ራዕይ

***"ፍፁሙን ሰዉ በመስራት የታደሰችና ገዥ ቤተክርስቲያንን በምድር ላይ መግለጥ።"***

ራዕያችን የነገ መድረሻችችን፤ የዛሬ እንቅስቃሴ ትኩረት እና ጉልበታችን ነዉ። የራዕያችን ምንጭ የፈለቀዉ በቆላስያስ ምዕራፍ አንድ ቁጥር ሃያ አምስት ሲሆን ከዚህ እንደሚከተለዉ ይነበባል፡-

***"እኛም በክርስቶስ ፍፁም የሚሆን ሰዉን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰዉን ሁሉ እየገሰፅን ሰዉንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከዉ እርሱ ነዉ።"***

ከክፍሉ እንደምንረዳዉ ሰዉ ፍፁም ሆኖ የሚሰራዉ በእግዚአብሔር ቃል ትምህርት ነዉ። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ፍፁም ሰዉ የሚሰራበት ወይንም የምንሰራበት ትልቁ መሳሪያችን ነዉ። የእዉነትና የህይወት ምንጭ በሆነዉ በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሳሪያነት፡- በመርህ የሚኖር፣ በአላማና በቃሉ ሃይል የተሞላ፣ በእግዚአብሔር ቃል ጥበብ በልቀት አእምሮዉ ከፍ ያለ ሰዉን መስራት እግዚአብሔር ለምርጦቹ 7000 ቤተክርስቲያን የሰጣት ራዕይ ነዉ።

ፍፁም ሰዉ ስንል በቃሉ ልክ የተሰራ፣ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ባህሪና ብቃት የተላበሰ፣ እግዚያብሔር ያሰበዉን የስብዕና መልክ በምድር አርዓያ ወይንም ማሳያ (PROTOTYPE) ሆኖ የሚገለጥ ሰዉ ማለታችን ነዉ። የአኗኗር፣ የአሰራር ባህል፣ መርህና እሴት በእግዚአብሔር መንግስት ባህል፣ መርህና እሴት በመለወጥ ለቤተክርስቲያን፣ ለምድርና ለትዉልድ ፍፁም መታደስ ይህች ቤተክርስቲያን ትተጋለች።

ገዥነት ስፍራ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለአካሉ (ለቤተክርስቲያን) የሰጣት ማንነት ነዉ።

## ተልዕኮ

የምርጦቹ 7000 ቤተክርስቲያን ተልዕኮ ከዚህ እንደሚከተለው ነው። ይህም፡-

- ቤተክርስቲያንን ማደስ \Reforming the Church\
- መንግስቱን ማስፋት \Expanding the kingdom\
- የእግዚአብሔርን መንግስት የፍቅር ማህበረሰብ መገንባት \Set up kingdom communities\
- በፍፃሜውም ምድርን ወይም ትውልድን መለወጥ \Transforming nations\ **(R.E.S.T.)**

ማቴ 13፤31 *“መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች፤”*

*የወንጌል ተልዕኮ በግለሰብና በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ብቻ የተወሰነ ህብረትን የምናደርግበት ጉዳይ አይደለም። እንደዉም በዋነኛነት ሁላችን እንደቤተሰብ በሰማያዊዉ የወንድማማችነታችን እዉቅና በጋራ የምንቀመጥበትና የምንሰራበት፤ ለትዉልዶችና ለህዝቦች ሁሉ የሚሆን ሰማያዊ ጥሪ ነዉ። ይሁንና በልዩ ልዩነት ላይ የተመሰረተዉ ህብር መንግስታዊ መገለጣችን፤ እንዲህ በዘር ደረጃና ጥቂት በሚመስል መለኮታዊ ጅማሬ የሚነሳሳም ነዉ። ቤተክርስቲያናችንም ካሉባት የግልና አጥቢያዊ አደራዎች ባሻገር፤ ለትዉልድና ለምድር የሚሆን መንግስታዊ ሸክሞችና ራዕዮችን ተቀብላለች። ይሁንና አተገባበራችን በምድሪቱ ያሉትን አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትና ህብረቶች ማንነትና አካሄድ በማይጋጭ መልኩና በጥንቃቄ ለማድረግ፤ ፈቃደኝነታቸዉን ከሰጧት አገልጋዮችና መሪወች ጋር በመመካከር በቅርበት አብራ በመስራት ላይ ነች።*

*በተጓዳኝም እንደዚህ እግዚአብሔር አስቀድሞ በመንፈስ ሸሽጎ በምድሪቱ ወዳዘጋጃቸዉ ቅዱሳን ልብ ራዕዮቹን በመዝራት ላይ ትገኛለች። ማን ያዉቃል የእርስዎስ በዚህ ታሪካዊ ጊዜ በምድሪቱ መገኘት ለዚህ አይነት መፅናናት እንደሆነ? ከሰማይ በመጣልን ‘የተቀጠረ ጊዜያችን’ የሚለቀቀዉን ፈዉስና በረከቶች፤ ወንድሞቻችን ሁላችሁ ፕሮግራሞቻችሁን ከወዲሁ አስተካክላችሁ በመገኘት እንድትችሉና፤ ብሎም ከፀሎት የሚጀምር መጠነ ሰፊ አብሮነታችሁን እንድናገኝ በማመን፤ ወደዚህ ታላቅ መንግስታዊ ድግስ በጌታ ፍቅር እናድማችኋለን።*

*የቤተክርስቲያኗ አብሮ ሰራተኞች*

# ማዉጫ

1ኛ ዓመት በዓል
‘የወንጌል ወንድማማችነት ሳምንት’

*ከተማ-አቀፍ ወጣቶችና የህፃናት ቤተክርስቲያን*

*የአባቶች በረከትን መቀበያ ልዩ ጉባኤ*




*ኦፕሬሽን ሉቃስ*

*የሽማግሌወች ጉባኤ*

*2014*
*የወንጌላዊያን አብያተ-ክርስቲያናት ካታሎግ*

# 1ኛ ዓመት በዓል



## *‘የወንጌል ወንድማማችነት ሳምንት’*

*መሳ 11፤40 ”የእስራኤልም ሴቶች ልጆች በዓመት በዓመቱ እየሄዱ የገለዓዳዊውን የዮፍታሔን ልጅ በዓመት አራት ቀን ሙሾ እንዲያወጡ በእስራኤል ዘንድ ልማድ ሆነ።”*

እግዚአብሔራዊም ሆኑ አለማዊ ልማዶችና በዓላት በአንድ ወቅትና ሁኔታ፤ በተወሰኑ ሰወች የሚጀመሩ ናቸዉ። በኋላ ግን በማህበረሰብ ሁሉ የመደረግ አቅምና ተወራራሽነት አግኝተዉ እንደባህል ይሆናሉ። ቤተክርስቲያን በመሰረታዊነት በምድር ያለችዉ በዙሪያዋ ያሉ አለማዊ ልማዶችና ባህሎች እንዳይወርሷት ለመከላከል አይደለም። ሰማያዊና መፅሃፍ ቅዱሳዊ የሆኑ የመንግስቱን ባህሎች በማምጣት ትዉልዷን ልታስተምርና ልታስለምድ እንጂ። ይኼ ግን በድንገትና ዝም ብሎ በመጠባበቅ የሚሆን አይደለም። ቅዱሳን አዉቀን፣ አስበንና አቅደን የምንጀምረዉና የምናሳድገዉ ልማድ ነዉ።

ማናቸዉም እግዚአብሔርን መምሰልንና ትዕዛዛቱን መፈፀምን የሚያስለምዱን ልማዶች ሁሉ ሰማያዊ ናቸዉ። ይሁንና ይህንን የማይወድ የዚህ አለም አምላክ፤ ቅዱሳን ባልነቃንበት ሁኔታ በመንፈሳዊ ተፅዕኖ ማስተዋላችንን አሳዉሮ፤ ተፃራሪና አጥፊ ልማዶችን ያስለምደናል። በተለይ ለቅዱሳን ልዩ ብድራትና ትርፍ ያላቸዉ፤ የአንድነትና የፍቅር ኑሮን እንዳንለምድ። መጥፎ ልማዶች የማንተባበራቸዉ ብቻ አይደሉም። በሌላ ጠቃሚና የሚያንፁ መፅሃፍ ቅዱሳዊ ልማዶች መተካት የሚያስፈልጋቸዉም ናቸዉ። ቅዱሳን ይህንን አስተዉለን፤ የሚለያየንን አንድ በሚያደርገን፤ የሚያጣላንን በሚያፋቅረን፤ የሚያራርቀንን በሚያቀራርበን ልማድ የመተካት ሃላፊነት የሁላችንም ነዉ። ዕብ 10፤25 *“በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።* በመሆኑም ቤተክርስቲያናችን አንድ አዲስ ባህልን በጣልያን ለምንገኝ ቅዱሳን ለማስለመድና፣ ለመጪዉም ትዉልድም ትቶ ለማለፍ፤ ከሚፈቅዱ አብያተ ክርስቲያናትና ቅዱሳን ጋር በመተባበር ለአንድ ሳምንት የሚቆይ መንፈሳዊ በዓል በመደገስ ላይ ትገኛለች።



*የወንጌል ወንድማማችነት ሳምንት 2014*። ክርስቶሳዊ ወንድማማችነታችንን እያንፀባረቅን፤ በአንድነትና በፍቅር መኖርን የምንለምድበት አዲስ ልማድ። የአንደኛ አመት በዓላችንን ከጁላይ 28 እስከ ኦገስት 3 2014 እ.አ.አ. በሮም via Tiburtina 994 በሚገኘዉ Istituto Salesiano Marchesa Gerini Torlonia ግቢ ዉስጥ ለማድረግ መሰናዶ ጀምረናል። በመላዉ



ጣልያን የሚኖሩና ይኖሩ የነበሩ ወንድሞቻችንን ጨምሮ፤ በዚህ አጋጣሚ ጣልያንን ለመጎብኘትና የዚህን አዲስ የመንግስቱ ልማድ ለመቅሰም የሚፈልጉ ወገኖች ከተለያየ ስፍራ ይታደማሉ።

በዓሉ በጣም ሰፊ ገፅታ ያለዉ የጋራ መድረክ ነዉ። <u>እንደ ግለሰብ</u> የተጠፋፋን የምንጎበኛኘበት፤ በአካል የማንተዋወቅ የምንተዋወቅበት፤ በፀጋ የምንተናነፅበት፤ ለፍቅርና ለመልካም ስራ የምንነሳሳበት፤ ስጦታና አድናቆታችንን የምንገላለፅበት፤ የስራ ዉጤቶቻችንንና አገልግሎታችንን የምናስተዋዉቅበት፤ መረጃ የምንለዋወጥበት፤ የጋብቻና የስራ መጣመሮች የሚፀነሱበት፤ ራዕዮቻችንንና ሸክሞቻችንን የምንከፋፈልበት፤ ለምድሪቱ ጠቃሚ ሃሳቦችንና እቅዶችን የምናንሸራሽርበት፤ በቅዱሳን ዘንድ ያለ የርስት ባለጠግነትን ቀርበን የምንነካበት፤ የምንመካከርበትና የምንደጋገፍበት፤ የምንገሳሰፅበትና የምንተራረምበት መድረክ ሲሆን፤ <u>እንደቤተክርስቲያንና እንደህብረትም</u> ለወንጌል እንቅፋት የሆኑ ነቀፌታወቻችንንና ችግሮቻችንን ለማስወገድ የምንመካከርበት፤ ለወንድሞቻችን ተጠያቂ በመሆን አካሄዳችንን ለጋራ ጥቅም በሚሆን ደረጃ የምናስታርቅበት፤ አጥቢያዊ አለመግባባቶቻችንን የምንፈታበት፤ በምድሪቱ የተጀመሩ አዳዲስ ህብረቶችና አጥቢያወች የሚተዋወቁበት፤ ለምድሪቱ በረከት ተደርገዉ የተሰጡ አገልጋዮችና ባለራዕዮች እዉቅና የሚያገኙበት፤ ለምድሪቱ መንፈሳዊ አባቶችና እናቶች አክብሮታችንን በመግለፅ በረከታቸዉን የምንቀበልበት፤ በፀጋ፣ በአገልግሎትና በአሰራር ልዩ ልዩነት ላይ የተመሰረተ ሰማያዊ አንድ አካልነታችንን የምናንፀባርቅበት፤ መንፈሳዊ መሪወችና አገልጋዮች፤ የመቀባበልና የአንድነት ምሳሌነታችንን ለምዕመናኖቻችን የምናሳይበት፤ ልዩ የፅድቅ መድረክ ነዉ።


በዉስጡም የተለያየ ይዘት ያላቸዉ ፕሮግራሞች ተካተዋል። የቀደሙ ኮንፈረንሶችና ታሪካዊ ክንዉኖችን የሚያስታዉሱ ፎቶወችና ፊልሞችን የምናገኝበት ኤግዚቢሽን፤ የአገልግሎትና የግል ሙያ ዉጤት የሆኑ ምርቶችና ስራወችን ለወንድሞቻችን በሽያጭ የሚቀርቡበት ባዛር፤ የአድራሻ ካርዶችና የማስታወቂያ በራሪ ፅሁፎቻችንን መለዋወጫ የመረጃ ዴስኮች፤ በምድሪቷ ቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ ላይ ወሳኝ ተግባርና ሃላፊነት ካላቸዉና ከነበራቸዉ ሰወች ጋር የሚደረግ የቃለ-መጠይቅ ጊዜ፤ የተለያዩ የስነ-ፅሁፍና የጥበብ ስራዎችን ማሳያ ኮንሰርት፤ የአምልኮና የእግዚአብሔር ቃል አገልግሎት ጊዜ፤ ወ.ዘ.ተ. ።

እንደእግዚአብሔር ፈቃድ ***“የሁለተኛ አመት የወንድማማችነት ሳምንት 2015 በዓል”*** ከሜይ 1 እስከ ኦክቶበር 31 2015 የሚደረገዉን የሚላኖ ኤክስፖን አስታከን፤ ሚላኖ ከተማ ላይ ከሚገኙ ቅዱሳንና አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመተባበር ለማድረግ እናስባለን። የፅድቅ ተፅዕኖ በማምጣት ትዉልዳችንን ለመንግስቱ ኑሮ ለማዘጋጀት እግዚአብሔር በላከልን በዚህ አዲስ ልማድ፤ ሌሎች ወንድሞቻችንንም በመጋበዝ፤ መገኘትና መሳተፍ ትችሉ ዘንድ ይህ ታላቅ እድል መኖሩን ከወዲሁ ልናበስራችሁ እንወዳለን።

ማቴ 22፤4 ***“እነሆ፥ ድግሴን አዘጋጀሁ፥ ኮርማዎቼና የሰቡት ከብቶቼ ታርደዋል፥ ሁሉም ተዘጋጅቶአል፤ ወደ ሰርጉ ኑ በሉአቸው አለ።”***

# ከተማ-አቀፍ

## የወጣቶችና የህፃናት ቤተክርስቲያን



ልጆች ለወላጆቻቸዉ ብቻ ሳይሆን ለቤተክርስቲያንም ጭምር የተሰጡ ስጦታወችና አደራወች ናቸዉ። ወላጆች ወደ ቤተክርስቲያን አምጥተዉ ልጆቻቸዉን በጉባኤ *'ለጌታ አሳልፈዉ የሚሰጡበት'* ስርዓት፤ በወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የተለመደ መፅሃፍ ቅዱሳዊ አካሔድ ነዉ። ይህም ልጆቹን የወላጆቻቸዉ ብቻ ሳይሆን የቤተክርስቲያን ስጦታወችም አድርጓቸዋል። ይኼ አካሔድ ቅዱሳንን እንደግለሰብና እንደቤተክርስቲያንን ስለተሰጡን ልጆች፤ ተጠያቂ በምንሆንበት አደራና ሃላፊነት ከወላጆቻቸዉ ጋር አስተሳስሮናል። በተለይ ከመንፈሳዊ ህይወታቸዉ አንፃር ሁላችን ድርሻና አደራ አለብን። የልጆቹ ጌታን ማወቅና በዉስጣቸዉ ያለ መለኮታዊ ስጦታ ለትዉልዳቸዉ መገለጥ፤ የወላጆቻቸዉ ብቻ ሳይሆን የሁላችንን ርብርቦሽ ይፈልጋል። ምን እንኳን በዚህ ረገድ የወላጆች ድርሻ የጎላ ቢሆንም።

ባለፉት አመታት እግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ ለምድሪቱ ቤተክርስቲያን በርካታ ልጆችን ሰጥቷል። ስንቶቹ በጌታ እንዳሉ? እና የስንቶቹ ስጦታ ትዉልዳቸዉን እየጠቀመ እንዳለ? ፍርዱን ለእናንተ እንተወዉ። ነገሮችን ለማስተካከልና ከስራቸዉ ለመለወጥ ግን ዛሬም አልረፈደብንም። ልጆቻችንን ከዘመኑ ጥፋት ማስመለጥና ጠቃሚ ዜጎችን እንዲሆኑ ማድረግ የምንችለዉ፤ ወደ ቃሉና መንግስቱ ስርዓት ይዘናቸዉ መሮጥ ስንችል ብቻ ነዉ። ድምፁንና መንፈሱን ለምደዉ የሚያድጉበት መድረክን በመፍጠር፤ በየቤተ ክርስቲያኖቻቸዉ ከሚያገኙት የእሁድ የህፃናት አገልግሎት በተጓዳኝ፤ ሌሎች መንፈሳዊ ግብዓት ያላቸዉ እድሎችን ስናመቻችላቸዉ። ለዚህም በየከተማዉ ምቹ አዳራሾችን በማፈላለግ፤ እንደየ እድሜ ክልላቸዉ የተከፋፈሉ፤ በፀጋ ሰወችና በባለሙያወች የታገዘ የወጣቶች ቤተክርስቲያን፤ ዘወትር ቅዳሜ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ለማስጀመር እናያለን። ይህም የማናችንም አጥቢያ አካል ሳይሆን ሁላችን በጋራ፤ ስለልጆቻችንና ስለመጪዉ ትዉልድ ያለብንን አደራና ሃላፊነት፤ ለመወጣት የበኩላችንን የምናበረክትበት የጋራ መድረክ የሚሆን ነዉ።

ይህ በእግዚአብሔርና በህሊና ተጠያቂ የምንሆንበትን አደራ ከማሰራቱም በላይ፤ በርካታ ጥቅሞችን ያስገኝልናል። በዋነኛነት ልጆቹ በእኛ ዘመን ያለዉን የመከፋፈልና ያለመቀባበል መልክ የሻረ፤ የህብረት መድረክን ለምደዉ እንዲያደርጉ ማስቻላችን፤ ነገ በእነሱ የአገልግሎት ዘመን መፅሃፍ ቅዱሳዊዉ አንድነታችን እንደቃሉ እንዲመለስላቸዉ ተስፋን ይዘራባቸዋል። በተጓዳኝም በፀጋ ሰወችና በባለሙያወች የሚሰጡ ትምህርቶችና ጠቃሚ ቁሳቁሶች፤ የየአጥቢያወቻችንን የእሁድ የህፃናት አገልግሎት የበለጠ ለዉጤታማነት ይደግፍልናል። ለልጆቹም ባላቸዉ ተሰጥኦና ዝንባሌ እንደነሱ አይነት ጓደኛና አጋር የሚያገኙበትን እድል ይበልጥ የሚያሰፋላቸዉ ሲሆን፤ አልፎ ተርፎም የትምህርት ቤትና የሰፈር ጋደኞቻቸዉን ከአምላካቸዉና ከህይወት እሴቶቻቸዉ ጋር የሚያስተዋዉቁበትና በፅድቅ ተፅዕኖ ማምጫ እድልን ይፈጥርላቸዋል። በአዉሮፓዉና በአፍሪካዊዉ አለም ባህልና አመለካከት መካከል ተገኝቶ፤ ግራ በመጋባት የተጠቃ ማንነታቸዉን በማከም፤ ሰማያዊ ማንነታቸዉን በእነሱ ሁኔታ የሚገልፁበትና የሚያንፀባርቁበት መድረክም ይሆንላቸዋል።




እግዚአብሔር የትዉልዶች አምላክ ነዉ። ስለሆነም ተተኪ ትዉልድን ማዘጋጀት የየትኛዉም ዘመን ቤተክርስቲያን ወሳኝ ሃላፊነት ነዉ። በዚህ ደረጃ ያልሰራች ቤተክርስቲያን በተዘዋዋሪ ወድቃለች። በመሆኑም የምድሪቱን ዜጎች በወንጌል እንደተስፋ ቃሉ ከመድረስ አንፃር፤ ቋንቋዉ ቋንቋቸዉ፣ ባህሉ ባህላቸዉ፣ ዜግነቱ ዜግነታቸዉ የሆኑ ልጆቻችንን መጠቀም ስልታዊና ዉጤታማ አካሄድ ነዉ። የቤተክርስቲያን ህፃናትና ልጆች ጉዳይ፤ እንደነገሩና እንደቻልን የምንሰራዉ ሳይሆን፤ ቅድሚያ በመስጠት እንደሚጠበቅብንና እንደሚያስፈልገዉ ለመስራት የምንተጋበት የጋራ ጉዳያችን ነዉ። በተለያዩ አጥቢያወች የታቀፉና ለልጆች አገልግሎት ልዩ ጥሪና ፀጋን የተቀበሉ የምድሪቱ ቅዱሳንን በማስተባበር፤ ሁሉም በጋራ የሚሰሩበትን መንግስታዊ እድል በማመቻቸት፤ ልምዳቸዉንና እዉቀታቸዉን አስተባብረዉ ለጋራ ጥቅማችን በጋራ የሚሰሩበት መድረክ ልናስገኝላቸዉ ይገባናል። በዚህም የሁሉም ፀጋና ጥበብ ተጨምቆ አገራቀፍ ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉ፤ የመሰልጠኛ መድረኮችና አጋዥ መሳሪያወችን ለማዉጣትም ያስችለናል። በዚህ የራዕይ መነፅር የእኛ ዘመኖቹ ዮሴፎችና ዳንኤሎች እርስዎ እየታዩዎት ይሆን?

# የአባቶች በረከትን መቀበያ ልዩ ጉባኤ



*ሚልክ 4፤5-6 "እነሆ፥ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ። መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፥ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል።"*

ለምድሮችና ለህዝቦች ሁሉ የሚሆን የእግዚአብሔር የጉብኝት ቀን እየመጣ ነዉ። ነቅተዉና ተዘጋጅተዉ ለጠበቁት ታላቅ የሚባል፤ ተዘናግተዉና ተዝረክርከዉ ለተገኙ የሚያስፈራ የተባለት የተቀጠረ ቀን። ከዚህ አንፃር ቀኑ እየመጣልን ይሁን እየመጣብን፤ ራሳችንን በመፈተሽ ልናስተካክልበት የሚገባ ወሳኝ አቅጣጫን ከላይ ያለዉ ቃል ይጠቁመናል። የአባቶችና የልጆችን የልብ ይዘት በመፈተሽ፤ የቀደመዉንና የአሁኑን ትዉልድ በመንፈስ ልብ ለልብ የማቀራረብ ወሳኝ ተግባር። ይህ የትዉልዶች ክፍተት ባልተደፈነበት ሁኔታ፤ የጌታ ወደ ህዝቡ መምጣት ለመባረክ ሳይሆን ለመርገም፤ ለማነፅ ሳይሆን ለማፍረስ፤ ለማዳን ሳይሆን ለማጥፋት ሆኖ ሊገለጥም እንደሚችል ያስጠነቅቀናል። ጉብኝቱ የቀደመዉና የአሁኑን ትዉልድ ከዉጭ ለታይታ በሚሆን ደረጃ ሳይሆን፤ ከልብ በሆነ እዉነተኛ መቀባበል መያያዝን ይሻል።

ለዚህም ሁላችንን እንዲያዘጋጀን ከጌታ ዘንድ የተላከልን የኤልያስ መንፈስና አሰራርም አለ። ከአባቶቼ አልበልጥም ብሎ በተስፋ መቁረጥ ለተቀመጡና ከምድር መወሰድን ለሚናፍቁ <u>'ልጅ ኤልያሶች'</u>፡- የሚያበረታ የሰማይ ግብዓትን (ባርኮትን) ተነሳና ተቀበል (1ኛ ነገስት 19) በማለት ልባቸዉን የሚያዘጋጅ፤ እንዲሁም ከነመጎናፀፊያቸዉ ሊወሰዱ ላሉ <u>*'አባት ኤልያሶች፡-*</u> ተተኪ የሆኑ ኤልሳወች አሉና መጎናፀፊያችሁንና ባርኮታችሁን ጣሉባቸዉ (2ኛ ነገስት 2) በማለት፤ ሁለቱንም ትዉልድ ለመንፈሳዊ ልዉዉጡ የሚያዘጋጅ መንፈስ። ሰጭና ተቀባይ ኤልያሶችን የሚያገናኝ የዝግጅት መንፈስ። የምድሪቱ ቀደምት አባቶች በቅንነት ልባዊ ባርኮታቸዉን የሚለቁበትና ልጆችም በትህትናና በማስተዋል የሚቀበሉበት ተግባራዊ መድረክ ደግሞ ይኸዉልዎ። ቅዳሜ ኦገስት 2 ከሰዓት ከ14፡00 ጀምሮ በሮም via Tiburtina 994 በሚገኘዉ Istituto Salesiano Marchesa Gerini Torlonia አዳራሽ ለዚህ የተጠራ ልዩ ጉባኤ አለን።

እስከ 2000 ዓ.ም እ.አ.አ. በተለያዩ ሰባት የጣልያን ከተሞች (ሮም፣ ሚላኖ፣ ፊሬንዜ፣ ቦሎኛ፣ ብሬሽያ፣ ቶሪኖና ቤርጋሞ) ተገኝተዉ ቤተክርስቲያናትን በመትከል ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉ ቀደምት የጣልያን አባቶችና ሌሎችም የክብር እንግዶች እኛን ለመባረክ ይገኛሉ። በበረከት ቃላቸዉ በኩል የሚለቀቅልንን ታላቅ ሃይል ለመገናኘት መስመር እንዲሆነን፤ እኛም አስተዉለን የአክብሮት ስጦታችንን ይዘን እንቀርባለን። አስቀድመን የገንዘብ ስጦታወችን በዕለቱ በሚታደለዉ ፓስታ ዉስጥ በማድረግ በአባቶቹ እግር ስር በማኖር ለእነሱ ያለንን ልባዊ አክብሮት እንደልጅ እንገልፅላቸዋለን። ይህም ለአባቶቹ ለእያንዳንዳቸዉ የግል ፍላጎቶች የሚከፋፈል ይሆናል። በመቀጠልም በከተማ፣ በአጥቢያ፣ በቤተሰብ ወይም በህብረት ደረጃ ልዩ ልዩ ስጦታወችን፤ ለምንፈልጋቸዉ አባቶች መርጠን መስጠት የምንችልበት ዕድልም ይኖራል። ከዚህ መለኮታዊ እድል ተጠቃሚ ለመሆን በማንኛዉም መልኩ ራሳችሁን እንድታዘጋጁና እንድታማጥኑ ከወዲሁ አጋጣሚዉ መኖሩን መጠቆም እንፈልጋለን።

የዚህን ልዩ መለኮታዊ አጋጣሚ መንፈሳዊ ጥልቀት ያስተዉሉ። ምናልባት ለብዙወቻችን በህይወት ዘመናችን ደግመን የማናገኘዉ ብቸኛ አጋጣሚም ሊሆን ይችላል። መንፈሳዊ ቅንብሩ በግለሰብና በአጥቢያ ደረጃ የታሰሩብን መንፈሳዊ ቋጠሮወች የሚፈቱበትና መለኮታዊ ራዕዮችና ተልዕኮዎቻችን በመላዕክት ፍጥነት የሚወነጨፉበት መንፈሳዊ የሃይል ምንጭ ነዉ። ከዚህ ቀደም በምድሪቱ በዉጤታማነት ሰርቶ የታየ የፀጋ መጎናፀፊያ ያላቸዉ ቀደምት የምድሪቱ አባቶች መንፈሳቸዉንና ፀጋቸዉን ሳይሰስቱ ያካፍሉናል። የአባቶች ባርኮት በምድር ላይ ሊገኝ ከሚችል ነገር ሁሉ በላይ የከበረና ዉድ የቤተክርስቲያን ትልቅ ግብዓት ነዉ። አባታዊ በረከትን የተቀበለ ትዉልድና ቤተክርስቲያን፤ ወሳኝ የሃይልና የስፍራ ሽግግርን ይሆንለታል። በመንፈስ ንቃት አስተዉላችሁና አንዳች ነገርን እንደምትቀበሉበት ጠብቃችሁ፤ በዕለቱ ከልብ ዝግጅት ጋር ትታደሙ ዘንድ ወንድሞቻችንን ሁሉ እንመክራለን።



*ዘፍ 49፤26 "የአባትህ በረከቶች ጽኑዓን ከሆኑ ከተራሮች በረከቶች ይልቅ ኃያላን ናቸው። ዘላለማውያን ከሆኑ ከኮረፍቶችም በረከቶች ይልቅ ኃያላን ናቸው እነርሱም በዮሴፍ ራስ ላይ ይሆናሉ፥*
*በወንድሞቹ መካከል አለቃ በሆነው ራስ አናት ላይ።"*

# ኦፕሬሽን ሉቃስ (Operazione Luca)




*ሉቃ 1፤1-4* ***“የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ፥ ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፥ በኛ ዘንድ ስለተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለሞከሩ፥ እኔ ደግሞ ስለተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ።”***

ሉቃስ በወቅቱ የፃፈዉ ለአንድ ግለሰብ (ለቴዎፍሎስ) ነዉ። ሆኖም ታሪኩን በሚገባ መርምሮና ተከታትሎ ለመፃፍ የሚያስነሳዉ መልካም ዕይታ (ራዕይ) ከጌታ ዘንድ ሆኖለት ነበር። ለዚህም ስራዉ የአይን እማኝ የነበሩ አገልጋዮችን አፈላልጎ በመጠየቅና በወቅቱ በበርካታ ሰወች የተፃፉ ታሪካዊ መዛግብትን በማገላበጥ እንዲተጋም አስፈልጎት ነበር። ከዛም ሁሉን በቅደም ተከተል በየተራዉ ማስቀመጥ። የመታዘዙና የትጋቱ ዉጤትም የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸዉን ሁለት መፅሃፍን ለትዉልዶች አስገኝቷል። *የሉቃስ ወንጌልና የሃዋሪያት ስራ መፅሃፍትን*። ታሪክ የቤተ ክርስቲያን ትልቅ ሃብት ነዉ። ምክንያቱም የታሪኩ ባለቤት እግዚአብሔር ስለሆነ። ታሪክ የነገሮችን መነሻና ምንጭ ያስጨብጣል። ከትላንት ስህተቶች መክሮ ያስተምራል። ሂደቶችንና ተግዳሮቶችን በማስገንዘብ የዛሬን ስፍራ ያስረግጣል። ብሎም ለነገ ስንቅና ተስፋ ሆኖም ያስተነብያል። ለዚህ ሁሉ ግን ታሪክ ሙሉ እንዲሆን እርግጡ መታወቅና መፃፍ ይኖርበታል። ሉቃስ ይህን ማድረግ መቻሉ በእግዚአብሔርና በትዉልድ ሁሉ (የእኛን ጨምሮ) ብፁዕ አድርጎታል። የሉቃስና የመሰሎቹ ታሪክን በሚገባ አጠናቅሮ ለትዉልድ የማስተላለፍ ሰማያዊ ባህል ደግሞ እኛም ልንወርሰዉ የሚገባን ነዉ።

***ኦፕሬሽን ሉቃስ*** እንደእነሱ የመፅሃፍ ቅዱስ ክፍል የሚደረግ ባይሆንም እንኳን፤ ነገር ግን ለእኛም ትዉልድ የተሰጠ ተመሳሳይ ራዕይ ነዉ። በጣልያን የምትገኘዋን የአበሻዋን (ኢትዮጵያዊና ኤርትራዊ) ወንጌላዊት ቤተክርስቲያንን አማክሎ መንፈስ ቅዱስ የሰራዉን ታሪክ፤ ከጅማሬዉ ጀምሮ አጠናክሮ ለትዉልድ የማስነበብ መልካም አደራ። ይህችን ሃዋሪያዊት ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር ከአመታት በፊት እንደ ቅንጣት በጣልያን ምድር ሲተክላት ለዘመን መጨረሻ ትንቢታዊ አላማዉ ማስፈፀሚያነት አቅዷት ነዉ። ለዚህም የምትበቃ ትሆን ዘንድ በብዙ ነገር ዉስጥ አልፋ ዛሬ ያለችበት መልክና ስፋት ጋር ደርሳለች። ይኼም ግን እቅዱ የተፈፀመበትና የመጨረሻ መልኳ እንዳልሆነ ግልፅ ነዉ።

ቤተክርስቲያኗ ታሪክ በሚከበርበት ህዝብና ምድር የተገኘች *'ታሪክ-አልባ'* አካል ሆናለች። ስለሌላት ግን አይደለም ስላልተፃፈላት እንጂ። ሁለንተናዋን የሚያዉቅላትና የሚያሳዉቅላት 'ሉቃሳዊ' ትዉልድ ገና አላገኘችም።  በእኛ ዘመን ከተዘረጋዉ ቴክኖሎጂ መስመርና ከስራዉ ስፋት አንፃር ጉዳዩ የአንድ ግለሰብ ወይም ብድን ብቻ መሆን አይችልም። በእነሉቃስ የነበረዉ አይነት እይታና ትጋት ያለዉ ትዉልድ ሁሉ እንጂ። ለእርስዎም ይኼ ታላቅ ሉቃሳዊ የአገልግሎት እድል፤ እነሆ ደጅዎን እያንኳኳ ነዉ። ከታች በተገለፀዉ የቤተክርስቲያናችን ዌብ ሳይት ወይም በኦፕሬሽኑ አብሮ ሰራተኞች እጅ በሚገኘዉ ቃለ-መጠይቅ የሚነሱትን ጥያቄወች በእዉነትና በግልፅነት በመመለስ፤ የዚህ ታላቅ የአገልግሎት እድል ተካፋይ ይሁኑ። አምላካችን ለእኛና በእኛ ያደረገዉን ለሰዉ ልጆች ሁሉ ልናወራ አደራ አለብንና። (ኢሳ 48፤20) ይህም ብቻ ሳይሆን ታሪካችንን መፃፋችንና መግለጣችን ወደ ትንቢታዊ መጨረሻችን የሚያፈጥነንና የሚያስቸኩለን መለኮታዊ ቅድመ ሁኔታም ጭምር ነዉ። ዕንባቆም 2፤2-3 " ***እግዚአብሔርም መለሰልኝ እንዲህም አለ፦ አንባቢው ይፈጥን ዘንድ ራእዩን ጻፍ፥ በጽላትም ላይ ግለጠው። ራእዩ ገና እስከ ተወሰነው ጊዜ ነው፥ ወደ ፍጻሜውም ይቸኵላል፥ እርሱም አይዋሽም ቢዘገይም በእርግጥ ይመጣልና ታገሠው እርሱ አይዘገይም።"***

ስራዉን ለጊዜዉ በማስተባበር እየሰራች ያለችዉ ቤተክርስቲያናችን ነች። ይሁንና ለስራዉ መቀላጠፍና ዉጤታማነት በየከተማዉ የኦፕሬሽኑ ተወካይ ተጠሪወችን እያዘጋጀን ነዉ። ስራዉ የሁላችን ታሪክና የትዉልድ ሃላፊነት እንደ መሆኑ መጠን፤ ለራዕዩ ዉጤታማነትና ሙሉነት፤ በምድሪቱ የምንገኝ አጥቢያወች፤ ህብረቶችና ግለሰቦችን የተቀናጀ የጋራ ተሳትፎን ይጠይቃል።  ከእርስዎም በማንኛዉም መልኩ ሊረዱንና ሊተባበሩን የሚችሉትን መረጃዎች ሁሉ እንዲያስገኙልን በአክብሮት እየጠየቅን፤ ለዚህ ኦፕሬሽን ያስፈልጋልና ይጠቅማል ብለዉ ለሚያምኑበት፤ በጣልያንና ከጣልያን ዉጭ ለሚገኝ አካል ሁሉ ሃሳቡን በማካፈል፤ አልያም ከታች በተገለፀዉ የቤተክርስቲያናችን ዌብ ሳይት ገብተዉ እንዲያገኙ በመጠቆም፤ መረጃ ለማሰባሰብ ተግባሩ እንዲያግዙንና እንዲያቀላጥፉልን በጌታ ፍቅር እንጠይቃለን። ጊዜዎንና ጉልበትዎን ሰጥተዉ ለዚህ መልካም ስራ አብረዉን ለመቆም ስለሚፈቅዱ ከልብ እናመሰግናለን።




*Web site:- Gospel Believers the Unique 7000 Church Rome*

*@ Home page:- Operation Luck PDF*

# የሽማግሌወች ጉባኤ



1 ቆሮ 6፤5-6 *"አሳፍራችሁ ዘንድ ይህን እላለሁ።*
***እንደዚህ ነውን? በወንድሞች መካከል ሽማግሌ ሊሆን የሚችል አንድ አስተዋይ ሰው በእናንተ ዘንድ አይገኝምን? ነገር ግን ወንድም ወንድሙን ይከሳል፥ ይህም በማያምኑ ፊት ይደረጋልን?"***

ቤተክርስቲያን በአለማዉያን ጉዳዮች ላይ ሳይቀር የምትፈርድ ሰማያዊ አካል ነች። ይሁንና ዛሬ በሚያሳፍር ሁኔታ ነገሩ ተገልብጦ፤ በአለማዉያን የሚፈረድብንና የሚፈረድልን ሆነናል። የቤተክርስቲያን የዉስጥ ገመና ከዚህ ቤተሰባዊ ስርዓት መታጣት የተነሳ፤ ሙሉ በሙሉ በማያምኑት ፊት የተገለጠ ሆኗል። ወንድም በወንድሙ ላይ፣ አጥቢያ በአጥቢያ ላይ ያለዉ ክስና ሙግት፤ በቤት ካለነዉ ይልቅ በዉጭ ባሉት ዘንድ ተሰምቷል። የምንሰብከዉና የምንኖረዉ የተጋጨ የሆነበት ይኼ 'የእኛ ሁኔታ' ደግሞ፤ እምነታችንም አምላካችንም በፊታቸዉ የተነቀፈ አስመስሎታል። ይህም ለወንጌል ስራ ትልቅ እንቅፋትና ጋሬጣ ነዉ። ከዚህ መሰናክል የተነሳ ብዙወች መሮጥ እየፈቀዱ እንዳይችሉ ሆነዋል። ለዚህ መወገድ ደግሞ፤ አስቀድመን በእጃችን ያለዉንና የተሰጡንን የመፍትሄ ቁልፎች፤ በማስተዋል ልናነሳቸዉ ያስፈልገናል።

ለትዉልድና ለቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ዉድ ስጦታ ሰዉ ነዉ። በዚህ ደረጃ ብናስተዉል የጣልያን አብያተ ክርስቲያናት፤ በሰዉም በእግዚአብሔርም ፊት ሽማግሌ ሊሆኑን የሚችሉ ዉድ ስጦታወች ከላይ ተሰጥተዉናል። *በሰዉ ፊት ማለት፦* ባላቸዉ የፀጋና የህይወት ምስክርነት፤ *በእግዚአብሔር ፊት ማለት፦* ለምድሪቱ ቅዱሳን ባላቸዉ የሃላፊነት መንፈስና የልብ ሸክም፤ እዉቅና ሰጥተን ልንቀበላቸዉ የሚገቡ 'አባት' ወንድሞችን ሰጥቶናል። ስለሆነም በአለማዉያን ፊት የተገለጠዉ አሳፋሪ መልካችን በክብር ይሸፈንልን ዘንድ፤ ያፈርንባቸዉ እነዚህ ወንድሞቻችንን አክብረን እንደምድሪቱ ሽማግሌወች ልንቀበላቸዉ ቃሉ ይመክረናል። 1ጴጥ 5፤5 "*. . . ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፥ . . .*"

ለጋራ ጥቅማችን ስንል ሁላችን እነዚህ ወንድሞቻችንን እንደምድሪቱ አባቶችና ሽማግሌወች ልንቀበላቸዉ፣ ልንሰማቸዉና ልንገዛላቸዉ የሚያስችለንን የትህትና ልብስ ልንታጠቅ ያስፈልገናል። ይህ አካሄድ ደግሞ ማናችንንም ቢሆን፤ ባጠፋንበትና በተሳሳትንበት ነገር ይቅርታ ከመጠየቅ በላይ የማያስከፍለን ሆኖ፤ በዉጤቱ ግን ወንጌል የሚሮጥበትና ብዙ ፀጋና ሃይልን የምንታጠቅበት እግዚአብሔራዊ ስርዓት ነዉ። ወንድሞች በወንጌል ገበታ ላይ አብረን የታደምነዉ በቀዳሚነት አብረን ለመስራት ሳይሆን ለመኖር ነዉ። ማር 3፤14 "*ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው፥ . .*

ስለሆነም አስቀድመን በፍቅሩ እንዳንኖር እንቅፋት የሆኑብንን የጠብና የመለያየት እርሾወች ከመካከላችን በማዉጣት፤ በልብ ንፅህናና በእዉነተኛ መቀባበል የጋራ ኮንፍረንሶችንና የወንጌል ስርጭቶችን ወደ ማድረግ መመለስ ይገባናል። በዉስጥ አንድነታችንንና መቀባበላችንን በማጥራት፤ ወደ ዉጭ በጋራ መታየታችን መፅሃፍ ቅዱሳዊ አካሄድ ስለሆነም ጭምር።




ይህም የሽማግሌወች ስርዓት በማያምኑ ሰወች ጆሮ የደረሱ አለመግባባቶቻችንንና ግጭቶቻችንን፤ ቤተሰባዊ ከለላ በመስጠት በዉስጥ የሚፈቱበትን መልክ ይመልስልናል። ብሎም አሁን ያሉት የአብያተ ክርስቲያናት ህብረቶች ሊፈቷቸዉና ሊቋጪቸዉ ያቃቷቸዉን የእርስ በእርስ ጉዳዮቻችንን እልባት ያስገኙልናል። ከዉጭ ሆኖ በሚያዝ የበላይነት መንፈስ ሳይሆን፤ ከዉስጥ ሆኖ ነቀፋወቹንና ችግሮቹን በሚካፈል የወንድምነት መንፈስ፤ የተጣሉን በማስታረቅ፣ ያጠፉ ይቅርታ እንዲጠይቁና እንዲያስተካክሉ በማስደረግ፣ የሳቱን በማስተማርና በመመለስ፣ የራቁን በማስጠጋትና በመቀላቀል፣ ወ.ዘ.ተ. አባታዊ ግብዓትን ለአንድነታችን ያስገኝልናል።

ለዚሁ ስራ መሰረት ከመጣል አኳያ፤ እግዚአብሔር ለምድሪቱ ስጦታ አድርጎ ከሰጣቸዉ ወንድሞች መካከል፤ የእኛ አቅም በፈቀደና የእነሱንም ፈቃደኝነት ባገኘን መጠን፤ በዚህ አመት በሚኖረን የወንድማማች ሳምንት አመታዊ በዓል ላይ እንደ ወንጌላዊ ኤርሚያስ ገልላት፣ እንደ ፓስተር መስፍን ጥላዮ፣ እንደ ፓስተር መላኩ ይገዙ፤ አይነት ሌሎቹንም የምድሪቱ አባቶችን ለማስመጣት በመስራት ላይ እንገኛለን። ይህም በምድሪቱ ያለን መሪወችና የህብረቶች ተወካዮች፤ በቀጣይ የጣልያን አብያተ ክርስቲያናት የህብረትና የአንድነታችን ጉዳዮች ላይ በጋራ ተቀምጠን የመመካከሪያና የመነጋገሪያ እድልን ይፈጥርልናል። ይህም እንደመንደርደሪያ ሆኖ መፅሃፍ ቅዱሳዊ የተሃድሶ ቅርፅና አቅም ያለዉ፤ ዉጤታማና ዘላቂ፤ ዘላለማዊ በረከትና ህይወት የሚገኝበት ህብረት እንዲኖረን ወደማስቻል ያራምደናል።



መዝ 133፤1-3 *“ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ፥ እነሆ፥ መልካም ነው፥ እነሆም፥ ያማረ ነው። . . . . በዚያ እግዚአብሔር በረከቱን ሕይወትንም እስከ ዘላለም አዝዞአልና።”*

# የወንጌላዊያን አብያተ-ክርስቲያናት ካታሎግ 2014



ወንጌል ከሰጠን ትልቅ ድልና ብልጫ አንዱ፤ በብዙ ወንድሞች መባረካችን ነዉ። ቅዱሳን በየትም ስፍራ የእኛ ብለን የምንገባበት ቤትና ወገኖቼ ብለን የምንጠራቸዉ ወንድሞች አሉን። በየከተማዉና በየስፍራዉ የጤነኛ ቤተክርስቲያናት መከፈትና የወንድሞች መኖር፤ ለእያንዳንዳችን ትልቅ የዋስትናና የብልጫ መንገድ እንደሆነም እናዉቃለን።  ይሁንና ማን የት እንዳለ? በቀላሉ ማወቅ የምንችልበት መንገድ ከሌለ፤ እያሉን እንደሌሉን ያክል፤ በጉድለትና በጥበት ለመመላለስ እንገደዳለን። ይህንን ያለመተያየትና ያለመተዋወቅ ጥበት ለመሻር፤ ቤተክርስቲያናችን ከዚህ አመት ጀምሮ አመታዊ ካታሎግ ለማዘጋጀት አቅዳለች። በሆነ አጋጣሚ አንድ ከተማ ቢገኙና ለሆነ ጉዳይ ወንድም ቢያስፈልግዎት፤ በቀላሉ ወንድሞችን መገናኘት የሚችሉበት አጭር መንገድ።

በዚህም ካታሎግ በየከተማዉ ያሉ አጥቢያወችና ህብረቶች ተጠሪወችና የማምለኪያ ስፍራዎቻቸዉ አድራሻ፤ እንዲሁም ሳምንታዊ ፕሮግራሞቻቸዉ የሚካተቱ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ረዳት መንፈሳዊ አገልግሎቶችና ክርስቲያናዊ ሙያና ንግድ ያላቸዉ ወንድሞቻችንም እንዲሳተፉ እንዲተዋወቁ እንፈልጋለን።  ከ100 ቃላት ያልበለጡ የፅሁፍ ማስታወቂያወችን በነፃ የምናስተናግድ ሲሆን በፎቶና በሌላም መንገድ የተስፋፉ ማስታወቂያ ለማስወጣት ለሚፈልጉ መጠነኛ ክፍያ ይኖረዋል። ይህ ግን የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን ማስታወቂያወች አይመለከትም። በዚህም ካታሎግ የሌሎችን መረጃ ማግኘት ብቻ ሳይሆን፤ በምድሪቱ ብቻቸዉን እንደቀሩና እየሰሩ እንዳሉ ለመሰላቸዉ ወንድሞቻችን፤ ራሳችንን፣ አገልግሎታችንን፣ ንግዳችንንና ሙያችንን በመግለጥ ልንገኝላቸዉም ያስፈልጋል። እግዚአብሔር የሚያያቸዉ፤ ለእኛ ግን ያልተገለጡልንና ያልተገናኘናቸዉ ብዙ ወንድሞቻችን፤ እዚሁ ጣልያን ምድር በተለያየ ስፍራ ተበታትነዉ እንዳሉት እናዉቃለን።



በዚህ ረገድ አገልግሎትዎንና ንግድዎን ለማስተዋወቅ የሚፈልጉ ከሆነ፤ የአገልግሎትዎን (የንግድ፣ ሙያዊ) ስምዎን፤ ሙሉ አድራሻ፤ የኢ-ሜይል ወይም ፌስብክ አድራሻና ስልክ ቁጥርዎን፤ ከዚህ ጀርባ በተጠቀሰዉ የኢሜይል አድራሻ በመፃፍ አልያም በስልክ SMS በማድረግ ማስመዝገብ ይችላሉ። ካታሎጉ ወደ ህትመት ስራ ከተላለፈ በኋላ የሚደርሱን አድራሻወች፤ በመጪዉ አመት 2015 ካታሎጋችን ላይ የምናካትታቸዉ ይሆናሉ።

# የ፲ኛ ዓመት በዓላችን

# የክብር ስፖንሰር ይሁኑ!!



*የ’ወንጌል ወንድማማች ሳምንት* ፕሮግራምን በተለያየ መልኩ ስፖንሰር ለማድረግ ለምትፈልጉ ወንድሞች፤ ቤተሰቦች፣ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትና ህብረቶች፤ ቤተክርስቲያናችን ከታች የተዘረዘሩትን እድሎችን አመቻችታላችኋለች። ስፖንሰር አድራጊወችም እንደሚመቻችሁ፤ ከታች በተጠቀሰዉ አድራሻችን በቀጥታ ለባንክ ገቢ በማድረግ፣ ወይም በቤተክርስቲያን የተዘጋጀዉን የፓስታ ቅፅ (Bollettini Postali) በመሙላት፤ ወይም በቀጥታ በአድራሻችን በመምጣት፤ ወይም የፕሮግራም አስተባባሪወችን ቀጠሮ በማስያዝ የቤተክርስቲያናችን ማህተም ያለበት ደረሰኝ በመቀበል ክፍያችሁን መፈፀም ትችላላችሁ። ከአንድ በላይ ስፖንሰር እንድታደርጉም ቤተክርስቲያን ታበረታታለች።

*1ኛ ደረጃ የክብር ስፖንሰር 1000.00 ኤዉሮ*

*2ኛ ደረጃ የክብር ስፖንሰር 500.00 ኤዉሮ*

*3ኛ ደረጃ የክብር ስፖንሰር 250.00 ኤዉሮ*

*4ኛ ደረጃ የክብር ስፖንሰር 100.00 ኤዉሮ*

*5ኛ ደረጃ የክብር ስፖንሰር 50.00 ኡዉሮ*

ከዚህም ዉጭ ከቀደምት አባቶችና ከክብር እንግዶች፤ የሚፈልጉትን ሰዉ የመጓጓዣና የማረፊያ ስፍራ ወጪ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመሸፈንም በቀጥታ መሳተፍም ይቻላል። በጉልበት፣ በምክርና በተለያየ መንገድ ከዚህ መልካም ስራ ጋር አብራችሁ ለመቆምና ለመባረክ ለምትፈልጉ ሁሉ፤ በስልክ ወይም በኢሜይል ቀጠሮ በማስያዝ ልታገኙንና ሁኔታወችን ልናመቻችላችሁ እንችላለን።

**Bonifico Bancario**: *Banca Monte dei Paschi di Siena* – Codice Filiale, 8721
IBAN: **IT 71 w 01030 03323 000000186159 -** C/C n. **000000186159**
ABI: **01030** - CAB: **03323**
Intestatario: **Chiesa Evangelici i Unici 7000**
C.F. **97781780586**

*መንግስትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን።*

# የቤተክርስቲያናችን መደበኛ ፕሮግራሞች

- ዘወትር ዕሁድ ከ10፡30 – 13፡30 የፀሎት፣ የአምልኮና የእግዚአብሔር ቃል አገልግሎት ጊዜ
- ዘወትር ሃሙስ ከ17፡30 – 19፡30 የመፅሃፍ ቅዱስ ጥናት
- ዘወትር ሰኞ የቤተክርስቲያናችን የፆምና የፀሎት ቀን
- የወሩ የመጨረሻ እሁድ ፕሮግራም ይዘት የነፃነትና የፈዉስ አገልግሎት
- የወሩ የመጀመሪያ እሁድ በመደበኛዉ ፕሮግራም ማብቂያ የጌታን ስጋና ደም በጋራ የምንወስድበት ጊዜ

## አድራሻችን


*Via Gerace 5, 00182 Roma*

*(Zona Metro A Re di Roma or Stazione Tuscolana)*

*E-mail:- U7000rome@gmail.com o abeitaly@yahoo.com*

*Tel:- 3889010756, 3203069883, 3460090578*

*Website:- Gospel Believers the Unique 7000 Church Rome*


በነፃ የሚሰጥ